## ከዶ/ር ብርሃኑ ነጋ "የነፃነት ጎህ ሲቀድ" መፅሃፍ ስለ ልደቱ አያሌው ውንብድና የሚተርከው ክፍል እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

…ፓርላማ መግባትን የሚደግፉት ኃይሎች ያላቸውን መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡ መከራከሪያው በዋናነት ኢህአዴግ ሊወስድ የሚችለው እርምጃ ቅንጅቱን ይጎዳዋል፣ ቅንጅቱ ያገኘውን የህዝብ ተቀባይነት ይዞ በፓርላማ ውስጥ የሕዝቡን ጩኸት እያሰማና አዲስ አበባን እያስተዳደረ ለሚቀጥለው የወረዳና የቀበሌ ምርጫ ቢዘጋጅ ይሻላል፡፡ ኢህአዴግ አሁን የተደናገጠ አውሬ ነው፡፡ ሥልጣኑን እንዳልተነካበት ሲያውቅ ትንሽ ቆይቶ ሊረጋጋ ይችላል፡፡ አንዳንድ መጠነኛ ለውጦችን ሊያደርግ ይችላል፡፡ እርግጥ ምርጫው ተጭበርበሯል፣ ሕዝቡም ድምጼ ይከበር እያለ እየጮኸ ነው፡፡ ቅንጅቱም በትዕግስት ኢህአዴግ በገባበት ቀውስ ተደናግጦ አገሪቱን ትርምስ ውስጥ ከሚከታት እኛ ሕዝቡን አረጋግተን ለሚቀጥለው ምርጫ ብናዘጋጀው ይሻላል የሚል ነበር፡፡

የዚህ አቋም ድክመት ከዚህ ቀጥሎ የሚኖሩት ምርጫዎች ዲሞክራሲያዊ ይሆናሉ ብለን የምናምንበት ምክንያት ይኖራል ተብሎ ለሚጠየቀው ጥያቄ በቂ መልስ መስጠት አለመቻሉ ነበር፡፡ ምክንያቱም ከምርጫ ማጣራት ሂደት መክሸፍ ጀምሮ ለኢህአዴግ የቀረበለት የመደራደሪያ ነጥብ በሙሉ ይህንን የወደፊቱን ዴሞክራሲያዊነት የምናረጋግጥበት መንገድ እንፈልግ የሚል ቢሆንም ሁሉንም አሻፈረኝ ብሏል፡፡ ኢህአዴግ አገሪቱን ወደ ቀውስ ሊከታት ይችላል የሚለው ሃሳብ እውነት አለው፡፡ ግን ፓርላማ በመግባት ይህንን ማዳን ይቻላል የሚለው አመለካከት እንደሚቻል የሚያሳይ ምንም ማረጋገጫ አልነበረውም፡፡ ዴሞክራሲ ያስፈለገው ይህን ቀውስ ለማዳን ነበር፡፡

ቅንጅቱ በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ መንግስት መለወጥ ይቻላል ብሎ፣ የትጥቅ ትግልን ተቃውሞ የሕዝቡን የነፃነትና የዴሞክራሲ ፍላጎት በከፍተኛ መጠን አሳድጎታል፡፡ ይህ ምርጫ ተካሂዶ የተሸነፈው ፓርቲ በጉልበቱ ሥልጣን ላይ የሚቆይ ከሆነና ሌሎቹ ፓርቲዎች ደግሞ ይህን ተቀብለው በፍርሃት ተቅለስልሰው ፓርላማ ከገቡ ለሕዝቡ የሚሰጠው መልዕክት በሰላማዊ መንገድ መንግስት መለወጥ ይቻላል የሚለው መልዕክት ተቃራኒ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ሕዝቡ በቁጭት የጦርነትን መንገድ እንዲመርጥ ይገደዳል፡፡ ይህ ደግሞ በምርጫው ምክንያት ተቀባይነቱን ካጣ መንግስት ደካማነት ጋር ተዳምሮ አገሪቱን የጦርነት አውድማ የማያደርግበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህ ፓርላማ በመግባት ሰላም ይመጣል የሚለው ምክንያትም ቢሆን ብዙም አሳማኝ አይደለም የሚል የተቃውሞ መከራከሪያ በሌላው ወገን ቀረበ፡፡

ይህ ክርክር በከፍተኛ ደረጃ ሲካሄድ ልደቱ አንድም ቃል አይተነፍስም ነበር፡፡ የእሱ ወገን መሆናቸው በግልጽ የሚታወቀው እነ ሙሼና ሌሎቹ ከኢዴአፓ-መድኅን የላዕላይ ምክር ቤት አባላት ደግሞ ከሁለቱም ወገን ሆነው ይከራከራሉ፡፡ ከቀድሞው መኢአድ ተወካዮችም ውስጥ በሁለቱም ወገን ሆነው የሚከራከሩ ነበሩ፡፡ እውነት ለመናገር ቅዳሜ ሙሉ ቀን በተደረገው ክርክር አንድ ወጥ የሆነ የቀድሞ ድርጅት ቅርጽ አይታይም ነበር፡፡ ሁሉም በቅንጅትና በልበ ሙሉነት የሚመስለውን ያቀርብ ነበር፡፡ ከመጀመሪያው በድምጽ አሰጣጥ ሂደት ላይ ካቀረብኩት ሀሳብ በስተቀር እኔም በፓርላማ መግባት ጉዳይ ላይ ምንም ሀሣብ ቀኑን ሙሉ አልሰጠሁም ነበር፡፡ በእረፍት ሰዓት እኔን ወደ አንዱ ወገን ለመሳብ የተወሰነ ቅስቀሳ (lobby) ይሞከር ነበር፡፡

በአንድ የእረፍት ሰዓት ሙሼ ወደ እኔ መጥቶ «ምነው ዝም አልክ አንተ እኮ እኛን ደግፈህ እንድትናገር እንጠብቃለን፤ አንተን ብዙ አባላት ስለሚሰሙህ የአንተ አቋምህን በግልጽ መናገር ይጠቅመናል» አለኝ፡፡ እኔም በመገረም «ሙሼ የእኔን አቋም ምን እንደሆነ እንዴት ታውቃለህ እውነቱን ልንገርህና እስከ አሁን ድረስ እኔ አልወሰንኩም፡፡ የሁለቱንም ወገን ክርክር በጥሞና እየሰማሁ ነው፡፡ እስከአሁን በሰማሁት ክርክር ግን የእናንተ ተቃራኒ ወገን የተሻለ ክርክር እያቀረበ ነው» አልኩት፡፡ ሙሼ በዚህ ደስተኛ አልነበረም፡፡ ለምን እንደሆነ ባላውቅም እኔ ከእነሱ ጋር እንደምወግን እርግጠኛ ነበር፡፡ የሚገርመው በማግስቱ እሁድ ጠዋት በታተመው የሪፖርተር ጋዜጣ «ብርሃኑና ልደቱ ፓርላማ መግባትን ይደግፋሉ» የሚል የመጀመሪያ ገጽ ዜና ወጣ፡፡ ይህ ጽሑፍ ሆን ተብሎ የወጣ እንደሆነ ገብቶኛል፡፡ በዚህ ሪፖርተር የልደቱ ጥብቅ ወዳጅ ሆኖ ነበር፡፡

ቅዳሜ ውይይቱ እንደሚያልቅ ግልጽ ነበር፡፡ ለእሁድ በተመሳሳይ ሰዓት ቀጠሮ ተወስዶ ነበር፡፡ እሁድም የውሳኔ መስጫ ቀን እንደሚሆን ተወስኗል፡፡ በአጋጣሚ ሆኖ ቅዳሜ ማታ እኔ በየዓመቱ የመስቀልን በዓል ምክንያት በማድረግ በቤቴ ትንሽ ግብዣ የማደርግበት ቀን ነበር፡፡ በዚህን ቀን ሁሌ እንደምናደርገው የቅርብ ጓደኞቻችንንና ወዳጆቻችንን እንዲሁም ዘመዶቻችንን እቤታችን ጠርተን ክትፎ በልተን ስንጫወት እናመሻለን፡፡ ከስብሰባው በኋላ በቀጥታ ወደ ቤት መሄድ ነበረብኝ፤ እንዲያውም በጣም አርፍጄ፡፡ ቀደም ብዬ ስልክ ደውዬ ባለቤቴን በስብሰባው ላይ ያሉትን ሰዎች ብጋብዝ በቂ ምግብ ይኖራል ወይ ብዬ ጠይቄአት አይጠፉም ብላኝ ስለነበር እዚያው ስብሰባው ላይ ሌላ ፕሮግራም የሌላችሁና እዚህ የነበረውን ክርክርና የእርስ በርስ ቅስቀሳ ክትፎ እየበላችሁ መቀጠል የምትፈልጉ ሁሉ ተጋብዛችኋል፡፡ ስብሰባ ውስጥ ከነበረው ሰው ከ20-25 የሚሆኑት ቤቴ መጥተው ነበር፡፡ አብዛኛዎቹ አባላት ቀደም ብለው ከነበሩት እንግዶች ጋር በመሆን ሲጫወቱ አንዳንዶቹ ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ ድምጽ የማሰባሰብ ሥራ ይሠሩ ነበር፡፡ እኔ በአብዛኛው ጊዜዬን ያጠፋሁት እንግዶቼን በመጋበዝ ነበር፡፡ በዚህን ምሽት በነበሩ ውይይቶች ምን ያህል ሰው ከቀድሞ አቋሙ እንደተቀየረ አላውቅም፡፡ ግን ሁኔታውን ከዳር ሆኜ ስመለከተው ቅንጅቱ የነበረውን ክፍትነት፣ ለውይይትና እርስ በርስ አቋም ለመለዋወጥ ይደረግ የነበረው ጤናማ ሙከራ በቅንጅቱ ላይ ያለኝን እምነት የበለጠ አጠናክሮልኛል፡፡

እዚህ ግብዣ መሀል ሆነን ቤቴን ከሚጠበቀው ዘበኛና የጎረቤት ዘበኞች በጣም ብዙ ቁጥር ያላቸው የደኅንነት ሰዎች መኪናዎች ቤቴን ከብበው መስፈራቸውን ሰማሁ፡፡ ከስብሰባው ስመጣ የተለመደው የሦስት መኪና ተከታይ በስተቀር ሌላ መኖሩን ሰማሁ፡፡ ለካስ ያን ዕለት እኔን ብቻ ሳይሆን በስብሰባው ላይ የተገኙትን የላዕላይ ምክር ቤት አባላት በሙሉ እየተከተሉ ሲያስፈራሩ ነው ያመሹት፡፡ ብዙ አባሎቻችን ደግሞ እኔ ቤት ስለመጡ ተከትለዋቸው መጥተዋል፡፡ ከምሽቱ አራት ሰዓት ጀምሮ እንግዶቼ አንድ በአንድ ወደየቤታቸው መሄድ ይጀምራሉ፡፡ ከቤቴ የወጡት ሰዎች በሙሉ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እየደወሉ በደህንነት ሰዎች ከፍተኛ ወከባ እየደረሰባቸው መሆኑን ይነግሩኛል፡፡ ወከባው ከሰው ሰው ይለያል፡፡ ፖለቲካው ውስጥ ምንም የሌሉበትን ጓደኞቼንና ዘመዶቼን ዝም ብለው ያስፈራሯቸውና ይሰድቧቸው ነበር፡፡ መልዕክቱም የሚመስለው «የብርሃኑ ጓደኛ ወይም ዘመድ መሆን አያዋጣህም» የሚል ነበር፡፡ የቅንጅት የላዕላይ ምክር ቤት አባላት የሆኑትን ግን በግልጽ በማስፈራራት አቋማቸውን ኢህአዴግ በሚፈልገው ዓይነት እንደሆነ ማድረግ ይሞክሩ ነበር፡፡ «እኛ የምንልህን ካላደርግህ የሚደርስህን እወቅ» የሚል የተራ ማፍያ ማስፈራሪያ ከመንግስት ደኅንነት መስሪያ ቤት ሰዎች ይቀርብ ነበር፡፡ ወደ መጨረሻ አካባቢ ከእኔ ቤት የወጡት እነ ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለ ማርያምና ኢንጅነር ግዛቸው ነበሩ፡፡ እነሱን የደኅንነት ሰዎች ቁም ስቅላቸውን ነበር ያሳዩዋቸው፡፡ በመንገድ መሄድ አልቻሉም፡፡ መሣሪያ እያወጡ እንገድላችኋለን እያሉ ከማስፈራራት አልፎ የሚሳደቡት የተለመደ ፀያፍ ስድብ በዚያ እድሜ ላሉ ሰዎች ለጆሮ የሚቀፍ ነበር፡፡ መሄድ ሲያቅታቸው ሕዝብ ባለበት ቦታ ብንገባ ይሻላል ብለው በቀጥታ ሂልተን ሆቴል ይገባሉ፡፡ እዚያም ተከትለዋቸው ገብተው ማስፈራራቱን ይቀጥላሉ፡፡ በመጨረሻም ምንም መነቃነቅ ሲያቅታቸውና ለሕይወታቸው በመፍራት ሂልተን ሆቴል የሚኖረውን የካርተር ማዕከል ወኪል ጆን ማርሽን ጠርተው ሁኔታውን ያሳዩታል፡፡ እነሱም የፈረንጆችን መሰብሰብ ሲያዩ ወጥተው ውጪ ይጠብቋቸዋል፡፡ በመጨረሻም እነ ዶ/ር ያዕቆብ በነ ጆን ማርሽ አጃቢነት በመከራ ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት አካባቢ ወደየቤታቸው ይገባሉ፡፡ ይህንን ታሪክ እኔ ጌቴ ሆኜ በስልክ እከታተል ነበር፡፡ እነሱ ቤታቸው ከገቡ በኋላ ነበር እኔም ወደ መኝታ የሄድኩት፡፡ ይህ የኢህአዴግን ድርጊት ግን እንቅልፍ ነሳኝ፡፡ እነዚህ ሰዎች ምንድነው የሚፈልጉት እስከመቼ አስፈራርተው መግዛት ይፈልጋሉ እንዲህ ዓይነት ፀያፍ ነገር ለማድረግ ምንም የማይቀራቸው ሰዎች እንዴት ነው የዴሞክራሲ ወገንተኛ የሚሆኑት ፓርላማስ ቢገባ በዚሁ በማስፈራራትና በጉልበት ከመግዛት ውጪ እንዴት አድርገው የሰውን ፍላጎት የሚያከብር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይገነባሉ እንደዚህ ዓይነት ማስፈራሪያ የአንድን የፖለቲካ ድርጅት ውሳኔ እነሱ በሚፈልጉት መንገድ ለመንዳት እንችላለን የሚል ለተቃዋሚው ከፍተኛ ንቀት እያሳየ ያለ ድርጅትና መንግስት ፓርላማ ስለተገባ ይህ አመለካከቱን ይቀየራል ተብሎ ይታሰባል የሚሉ ጥያቄዎች በአእምሮዬ ሲጉላሉ አደሩ፡፡

ጠዋት ከእንቅልፌ ስነሳ በመጀመሪያ ለባለቤቴ ፓርላማ መግባት የለብንም የሚል አቋም እንደያዝኩና ለዚህም የገፋፋኝ የማታው ድርጊት እንደሆነ፣ ይህም ያሳየኝ ኢህአዴግ ፓርላማ እንድንገባ የፈለገው ከምንም በላይ ለዴሞክራሲ ብሎ ሳይሆን ቅንጅቱን ከሕዝቡ ጋር ለማጣላት ነው የሚል መደምደሚያ ላይ በመድረሴ እንደሆነ ነገርኳት፡፡ ፓርላማ መግባት ትርጉም የሚሰጠው ኢህአዴግ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት

ተገገር ለመሆን ከወሰነ ብቻ እንደሆነና ይህንንም መወሰኑን የሚሳያው ቅንጅቱ አነስተኛ ያላቸውን የዴሞክራሲ ግንባታ ጥያቄዎች ከተቀበለ ብቻ ነው የሚል ውሳኔ ላይ ደረስኩ፡፡ ይህንን አቋም በግልጽ ለመከራከርም በቀጥታ ወደ ቅንጅቱ ስብሰባ ሄድኩ፡፡

የእሁዱ ስብሰባ ቅዳሜ የተጀመረውን ክርክር በመቀጠል ተጀመረ፡፡ ምሽቱን የኢህአዴግ ደጎንነቶች ሲሠሩ ያመሹትን ነገር ከስብሰባው በፊት ሁሉም እየተነጋገረበት ነው፡፡ እኔ ማታውን ሳሰላስላቸው የነጥቦች በሌሎችም አባሎች ነበሯቸው ያደርጉት ጉዳይ በብዙ ሰው ጭንቅላት ውስጥ ሲነሱ አድረዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ለተቃዋሚው፣ ከእነሱ የተለየ ሀሳብ ላለው ሰው ሁሉ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምንም ክብር የሌላቸው ትዕቢተኞች ናቸው የሚለው ስሜት በብዙ ሰው ውስጥ እየደነደነ ነበር፡፡ ውይይቱ የተወሰነ ደረጃ ከሄደ በኋላ እኔ ተራ ጠብቄ ያለኝን አመለካከት ተናገርኩ፡፡ ሃሳቤ በአጭሩ የቅንጅቱ ውሳኔ ቁርጥ ያለ መሆን እንደሌለበት፤ በመጀመሪያ በግልጽ ማስቀመጥ ያለብን የቅንጅቱና የሕዝቡ ጥያቄ ምንድንነው የሚለውን መሆኑን በእኔ እምነት ይህ ጥያቄ የዴሞክራሲ ግንባታ ጥያቄ እንደሆነ ይህ እንዲሆን ደግሞ ሊሟሉ የሚገባቸው ነገሮች ምን እንደሆኑ እነዚህ ነገሮች ከተሟሉ ወይም እነዚህ ጉዳዮች ላይ ቀናና እውነተኛ ድርድር ከተካሄደ ብቻ ፓርላማ እንደምንገባ በግልጽ ማስቀመጥ «እንገባለን» ወይም «አንገባም» ከሚለው ደረቅ አቋም የተሻለ ይሆናል፤ ለድርድርም በር ይከፍታል፣ እነዚህ ነጥቦችም ዋና የመታገያ መስመሮቻችን ይሆናሉ የሚል ነበር፡፡ ብዙው ተሰብሳቢ አንድ መካከለኛ መንገድ እየጠበቀ ነበር፡፡ አንዴ ይህ አቋም ከቀረበ በኋላ ብዙ ተወካዮች ይህንን አካሄድ በመደገፍ፣ የቀረበውን ሀሳብ የበለጠ እያከረሩ ተናገሩ፡፡

ይህን ሀሳብ የሚቃወም ከሁለቱም ወገን አልቀረበም፡፡ እነዚህ ለመግባት ያስፈልጋሉ ያልናቸው ሁኔታዎች ምን ምን መሆን እንዳለባቸው ሃሳቦች እየተሰጡ ነበር፡፡ በአካሄድ ደረጃ በመጀመሪያ በሃሳቡ ላይ ድምጽ ይሰጥበት ተብሎ በድምጽ አሰጣጡ ላይ ትንሽ ውይይት ተካሄደ፡፡ ሃሳቡን የሚቃወም ከሌለ በሙሉ ድምጽ (በኮንሴንሰስ) እንዳለፈ እንውሰደው ተባለ፡፡ በዚህን ጊዜ የለም ድምጽ መሰጠት አለበት የሚል ሃሳብ ቀረበ፡፡ በዚህን ጊዜ ሃሳቡን የሚደግፍ ተብሎ ወደ 53 ሰው አካባቢ ድምጽ ሰጠ፡፡ የሚቃወም ሲባል ምንም አልነበረም፡፡ ድምፀ ተዓቅቦ ሲጠየቅ ለደቱ ድምፀ ተዓቅቦ መጠየቅ የለበትም ብሎ አምርሮ ተከራከረ፡፡ ውሳኔው በድምጽ ብልጫ ሳይሆን በሙሉ ድምጽ ስለተወሰነ ድምፀ ተዓቅቦ መጠየቅ አግባብ አይደለም አለ፡፡ ነገር ግን እሱ ድምፁን በግልጽ እንዲሰጥ የፈለጉት ሰዎች በዚህ የቴክኒክ መከራከሪያ ሊተውት አልፈለጉም ነበር፡፡ ግን ገና ብዙ ሥራ ስለሚቀርና ዋናው ጉዳይ ቢወሰንም የሚቀርቡት አስፈላጊ ሁኔታዎች መዘርዘር ስለነበረባቸው አላስፈላጊ አተካሮ ውስጥ ላለመግባት ሲባል ውሳኔው በዚሁ ተቋጨ፡፡

ቀጥሎ የነበረው የአስፈላጊ ሁኔታዎች መዘርዘር ላይ የነበረው ብቸኛ ክርክር የ299 መቀመጫዎች የማጣራት ሁኔታ ይካተት ወይስ አይካተት የሚለው ነበር፡፡ በዚህ ላይ ቅንጅቱ በኋላ ላይ ያቀፈውና «የመጨረሻ አነስተኛ» ጥያቄዎች ያላቸው ላይ ማተኮር ይሻላል፡፡ አሁንም ኢህአዴግ ላለመደራደር ምክንያት እንዳያመጣ እሱን ጥያቄ መተው ይሻላል የሚለው ክፍል አሸንፎ ቅንጅቱ ለዴሞክራሲያዊ ግንባታ መሠረት ናቸው ያላቸውን ስምንቱን ጥያቄዎች ላይ ተስማማ፡፡ ይህንን የሚመለከት አጠቃላይ

መግለጫ የሚያዘጋጁ አንድ ኮሚቴ ተሰይሞ እሱን ያዘጋጃል፡፡ የቅንጅቱ አራት መሪዎች የጋዜጣዊ መግለጫውን እንዲሰጡ ይወሰናል፡፡
ይህ ሁሉ አልቆ ስብሰባው ሊበተን ሲል ሁልጊዜም የራሱን ጉዳይ ማዕከል የሚያደርገው ልደቱ ዛሬ በሪፖርተር ላይ የወጣውና ልደቱ ፓርላማ እንግባ ይላል የሚለው ወሬ ሆን ተብሎ እኔን ከሕዝቡ ጋር ለማጣላት የሚደረግ የተቀነባበረ ሴራ ስለሆነ ቅንጅቱ በጋዜጣዊ መግለጫው ላይ ይህንን እንዲያስተባብልልኝ ብሎ ይጠይቃል፡፡ ጋዜጣው ላይ የወጣው የሁለታችንም ስም ሆኖ እሱ ለምን ማስተባበል እንዳስፈለገው ግልጽ አልነበረም፡፡ የልደቱን ስሌት የሚያውቁ ወጣቶችም ይህንን ተቃውመው ነበር፡፡ ቅንጅቱ የግለሰቦችን ጉዳይ ሲያስተባብል የሚገኝበት ምክንያት የለም፡፡ እነዚህ ወጣቶች ልደቱ ደግሞ በፓርላማ የመግባት አቋም ነበረው፤ በስብሰባው ላይ ጓዶቹ ይህን ሲያንፀባርቁ ነው የዋሉት፡፡ በኋላ ሃሳባቸውን ቀይረው ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ይህንን ወሬ ብለን የምናስተባብልበት ምክንያት የለም የሚል አቋም ይዘው ነበር፡፡ ግን በጊዜው የነበረውን ጥሩ መንፈስ ላለማባላሸት በሚል አስተባብሎለት ተብሎ ተወሰነ፡፡
የፓርላማ አለመግባት ውሳኔ ሲወሰን የአዲስ አበባ ነገር ግልጽ የሆነ ውይይት አልተካሄደበትም ነበር፡፡ ቅንጅቱ ፓርላማ ላለመግባት ሲወስን የአዲስ አበባ ነገር እንዴት ይሆናል ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ ከዚህ በፊት የቅንጅቱ የአዲስ አበባ ተመራጮች ስለ ከተማው ርክክብ ለመነጋገር ማዘጋጃ ቤት በሄዱ ጊዜ «ፓርላማ ካልገባችሁ አዲስ አበባን መረከብ አትችሉም» ተብሎ በግልጽ በአቶ አርከበም በማዘጋጃ ቤቱም የሕግ ክፍል ኃላፊ የምርጫ ቦርድ ወኪሎች ባሉበት ተነግሮ ስለነበር ከዚያ በመነሳት ፓርላማ ካልተገባ አዲስ አበባን አያስረክቡም ተብሎ ለስብሰባው ተነግሯል፡፡
አዲስ አበባን ካሸነፍን ጀምሮ በቅንጅቱ በኩል ከተማውን ለመረከብ ብዙ ዝግጅቶች ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በመጀመሪያ ቅንጅቱን የሚወክሉት ሰዎች ለመወሰንና ከተማውን የሚያስተዳድሩትን ሰዎች ለመምረጥ ለአዲስ አበባ ምክር ቤት የተመረጡ አባሎች በሙሉ በተገኙበት፣ የምረጡን ዘመቻዎች ተደርጎ ምርጫ ተካሂዷል፡፡ በዚህም ምርጫ (የካርተር ማዕከል ታዛቢዎች በተገኙበት) እኔ በከንቲባነት፣ ዶ/ር አድማሱ በምትክል ከንቲባነት፣ አቶ አሰፋ በአፈ ጉባዔነት፣ ወ/ሮ ሸዋዬ ኪሮስ በምክትል ከንቲባነትና አቶ አንተነህ በዋና ፀሐፊነት ተመርጠናል፡፡ ከእኔ በስተቀር አራቱ ነባሩ ማዘጋጃ ቤት ሄደው ከነአቶ አርከበ ጋር ስለ ርክክቡ የተነጋገሩት፡፡ እዚህ ስብሰባ ላይ ደግሞ በግልጽ ፓርላማ ካልገባችሁ አዲስ አበባን አትረከቡም ተብለዋል፡፡ ይህን የመጨረሻው አልነበረም፡፡
የላዕላይ ምክር ቤቱ የፓርላማ አለመግባቱን ውሳኔ ሲወስን ውሳኔው አዲስ አበባንም እንደሚያጠቃልል አውቋል፡፡ ይህን ያወቀው ግን ፓርላማ ሳይገባ አዲስ አበባን የሚያስረክቡ ቢሆንም አንረከብም ከሚል አልነበረም፡፡ ሁለቱ የማይነጣጠሉ ውሳኔዎች ናቸው ከሚል መነሻ እንጂ፡፡
በማግስቱ መስከረም 30 ጠዋት ከአዲስ አበባ ተወካዮች ለአንዱ ከምርጫ ቦርድ ተደውሎ አዲስ አበባን ለመረከብ እየተዘጋጃችሁ ነው ወይ የሚል ጥያቄ ሲቀርብለት በመገረም ፓርላማ ካልገባችሁ አናስረክብም ብላችሁ የለም ወይ ብሎ ሲጠይቀው አይ ስለምናስረክባችሁ ማዘጋጃ ቤት እንድትመጡ ይለዋል፡፡ ይህንን ጊዜ የቅንጅቱ ተወካይ የምርጫ ቦርዱን ሰው የምትሉን የእውነታችሁን ከሆነ ለብርሃኑ ደውለህ

ንገረው ይለዋል፡፡ ከዚያም ልጁ ለእኔ ደውሎ ይነግረኛል፡፡ እኔም ዝም ብለው ሲቀልዱብህ ነው እንጂ በምንም ዓይነት አያስረክቡም፤ ለማንኛውም ወደ ቢሮ እየመጣሁ ስለሆነ ዋና ዋና ተመራጮች ቢሮ እንዲመጡ ንገራቸውና እዚያ እንነጋገራለን ብዬ ስልኩን ከመዝጋቴ እንደገና ይደወላል፡፡ የደወለልኝ የምርጫ ቦርዱ ኃላፊ አቶ ተስፋዬ መንገሻ ነበር፡፡ እሱም አዲስ አበባን ለመረከብ እንድትችሉ በ3፡30 ማዘጋጃ ቤት እንድትመጡ ይለኛል፡፡ እኔም አቶ ተስፋዬ የማታ ውሳኔያችንን አልሰማህም ወይ ቅንጅቱ እኮ ፓርላማ ላለመግባት ወስኗል፡፡

ከዚህ በፊት አንተ ባለህበት እነ ዶ/ር አድማሱን ልከን ፓርላማ ካልገባችሁ አዲስ አበባን አትረከቡም ብለው እነ አቶ አርከበ ሲናገሩ ሰምተን የለም ወይ እንዲያውም በጊዜው የርክክቡን ሂደት ለመጀመር ጠይቀን በፓርላማ ላይ ሳትወሰኑ ይህንንም ሂደት አንጀምርም ብለውን አልነበ ሁለቱን የሚያጣምር ሕግ አለ ወይ ተብለህ ተጠይቀህ አንተም ሆንክ የሕግ ክፍል ኃላፊው ኢህአዴግ (ጠቅላይ ሚኒስትሩ) ካልፈቀደ አትረከቡም አላልከንም ወይ አሁን ኢህአዴግ ሃሳቡን ቀየረ ወይ ብዬ ጠየቅሁት፡፡ አቶ ተስፋዬም እኔ ይህን ዝርዝር አሁን ላወራህ አልችልም፡፡ አስረክቡ ተብለናል ለማስረከብ ዝግጁ ነን፣ ማዘጋጃ ቤት እንድትመጡ፣ እስከዚያ ግን ወኪሎችህን ላክና ስለ ርክክቡ ሥነ-ሥርዓት እንነጋገር ይለኛል፡፡ እኔም ጥሩ፣ ወኪሎቻችን ማዘጋጃ ቤት በግማሽ ሰዓት ይደርሳሉ ብዬው ወዲያውኑ አቶ ኃይሉ ሻውል ጋር ደወልኩና የሆነውን ነገርኩት፡፡ እሱም አዲስ አበባን ፓርላማ ሳንገባ ካስረከቡንማ መረከብ አለብን፡፡ አሁኑኑ የላዕላይ ምክር ቤት ስብሰባ ይጠራና የትላንቱ ውሳኔ አዲስ አበባን መመልከት አለመመልከቱን አጥርተን ይመለከተዋል ቢባል እንኳን በተሰጠው የመረጃ ስህተት ላይ የተመረኮዘ (ማለትም ፓርላማ ከተገባ አያስረክቡም) ስለሆነ በአዲሱ መረጃ ላይ በመመርኮዝ ውሳኔ ይሰጣል ብሎ ቢሮ ደውሎ አስቸኳይ ስብሰባ ለማስጠራት ተስማምተን እኔ ወደ ቢሮ እሄዳለሁ፡፡ መንገድ ላይ እያለሁ ግን ወ/ሮ ሸዋዬ (የምክር ቤቱ ተመራጭ ምክትል አፈ ጉባዔ) ጋር ደውዬ አቶ አሰፋን፣ አቶ አንተነህንና ከተገኘ ዶ/ር አድማሱን አለበለዚያ ሌሎች አንድ ሁለት ተመራጮችን ይዘሽ ማዘጋጃ ቤት ሂጂና ስለ ርክክቡ ሥነ-ሥርዓት ተነጋገሩ፣ እስከዚያው ድረስ ደግሞ ቢሮ ደውለሽ በፀሐፊዎች በኩል በሙሉ የአዲስ አበባ ተመራጮች አሁኑኑ ቢሮ እንዲሰበሰቡ መልዕክት አስነግሪ ብዬ እኔ ወደ ቢሮ አመራሁ፡፡ ቢሮ ስደርስ ትልቁ አዳራሽ ውስጥ የአዲስ አበባ ተመራጮች እየተንጠባጠቡ እየገቡ ነበር፡፡ የቅንጅቱ ሥራ አስፈፃሚ ሰዎችም ለስብሰባ እየመጡ ነበር፡፡ ላዕላይ ምክር ቤቱ እስኪሰበሰብ ድረስ የአዲስ አበባ ተመራጮች ከግማሽ በላይ ሞልተው ስለነበር ዝም ብለው ከሚቀመጡ ብዬ ከተማውን በመረከብ ዙሪያ ውይይት ጀመርን፡፡

በመጀመሪያ ለምክር ቤቱ አባሎች ያነሳሁት ጥያቄ ከፓርላማ ውሳኔ አንፃር ተረከቡ ብንባል መረከብ አለብን ብላችሁ ታምናላችሁ ወይ የሚል ነበረ፡፡ ሀሳቦች ከሁለቱም በኩል እየተሰጡ እያለ ነበር የመጣ የመሰለኝ፡፡ ወዲያው ግን የእኛን ስብሰባ መድረኩ ላይ ተቀላቀለ፡፡ በአዲሱ የቅንጅት መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ምክትል ሊቀመንበሩ የተመራጮችን ጉዳይ ይከታተላል፡፡ በዚያ ኃላፊነቱ መሠረት እንደተገኘ ነግሮን ስብሰባው ቀጠለ፡፡ በዚህ ጊዜ ልደቱ አንድ በጣም አስገራሚ ነገር ተናገረ፡፡ በአዲስ አበባ መግባት ጉዳይ ቅንጅቱ ትላንት ወስኗል፡፡ ንግግሩ ኢህአዴግ አስረከበም አላስረከበም አዲስ አበባን መረከብ አትችሉምና ይህ አስፈላጊ ስብሰባ አይደለም የሚል

አንደምታ ነበረው፡፡ እኔም የለም ቅንጅቱ አዲስ አበባን ኢ.ህአዴግ አላስረከብም በማለቱ እንጂ ቢ.ያስረክብ ኖሮ የቅንጅቱ አቋም ምን ሊሆን እንደሚችል ከትላንትናው ስብሰባ መወሰን አይቻልም፡፡ ለዚህም ነው ሊቀመንበሩ ድንገት ምርጫ ቦርድና ኢ.ህአዴግ ለማስረከብ ከወሰኑ ቅንጅቱ የአዲስ አበባን ጉዳይ በግል ይወስን ብለው አስቸኳይ የላዕላይ ምክር ቤት ስብሰባ የጠሩት ብዬ መልስ ሰጠሁ፡፡ ልደቱ ግን በፍጹም አይሆንም አለ፡፡ ፓርላማ አንገባም ተብሎ አዲስ አበባ ሊገባ አይችልም ሲል በምሬት ተናገረ፡፡ ይህ አቋምህ ተብሎ አዲስ አበባ ሊገባ አይችልም ሲል በምሬት ተናገረ፡፡ ይህ አቋምህ ትክክል ሊሆን ይችላል፣ ቢሆንም ግን ላዕላይ ምክር ቤቱ አውቆ መወሰን አለበት፡፡

Source:ethioblogger.net